Public Health
Seattle & King County

# መጫወቻዎችን ማጽዳት በሽታን ለመከላከል ይረዳል



ህፃናት ገና በጅማሮ የትምህርት ፕሮግራም መጫወቻዎችን ሲጋሩ በሽታ አምጪ ተሕዋስያን በቀላሉ ሊዛመቱ ይችላሉ። መጫወቻዎችን ማጽዳት እና ቆሻሻቸውን ማስወገድ ተላላፊ በሽታዎች እንዳይስፋፉ ለመከላከል ይረዳል።

## የሚመከሩ ቅደም ተከተሎች

- አዲስ መጫወቻ ሲገዙ፣ በተቻለ መጠን ሊታጠቡ የሚችሉ መጫወቻዎችን ይምረጡ።
- ቀኑ ሲያልፍ አሻንጉሊቶች በሚቆሸሹበት ጊዜ ይሰብስቡ።
  - "በ አፍ የተያዙ" አሻንጉሊቶች – በአንድ ህፃን አገልግሎት ላይ ከዋሉ በኋላ
  - ሁሉም ሌሎች አሻንጉሊቶች – በየእለቱ፣ ወይም እንዳስፈላጊነቱ
- መጫወቻዎችን በተለያዩ መያዣዎች ውስጥ ይከፋፍሏቸው፡- አንድ ለጨርቅ መጫወቻዎች፣ ሌላ ደግሞ ለእንጨትና ለፕላስቲክ መጫወቻዎች። አሻንጉሊቶችን አስቀድሞ መደርደር ለማጠብና ቆሻሻቸውን ለማስወገድ ቀላል ያደርጋቸዋል።
- በቀኑ መጨረሻ፣ ወይም በተወሰነ ጊዜ (ለምሳሌ በእንቅልፍ ጊዜ) መጫወቻዎቹን ያጽዱ፣ ይጠቡ፣ እንዲሁም ቆሻሻ ያስወግዱ።
- የልብስ ማጠቢያ ማሽን፣ የእቃ ማጠቢያ ማሽን፣ ወይም እጅ በመጠቀም መጫወቻዎችን ማጠብ ይችላሉ።

## መጫወቻዎችን በእጅ ማጠብ

### ደረጃ 1:- ያጽዱ

- መጫወቻዎችን በደንብ በሳሙና ወይም በንፁህ ማድረጊያ እና በትኩስ ውሃ በማጠብ እርጥብ ቆሻሻ፣ ላብ እና አቧራ፣ እና ምራቅ ያስወግዱ። **መጫወቻዎችን በምናፀዳበት ጊዜ በጣም አስፈላጊው እርምጃ ነው።**
- የመጫወቻዎችን ቆሻሻ ከማስወገድ በፊት **ማጽዳት** አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ቆሻሻ ከማስወገጃው በንጹህ ቦታዎች ላይ ጀርሞችን በተሻለ ይገድላል።

### ደረጃ 2:- ማጠብ

- የመጫወቻዎችን ንጹህ ገጽታ ለመፍጠር ቆሻሻን፣ የሳሙና ቅሪቶችን፣ እና ጀርሞችን ለማስወገድ በውኃ ይጠቡ።

### ደረጃ 3:- ቆሻሻ ማስወገድ

- **ቆሻሻ ማስወገድ** ጀርሞችን ከገጽታ ወደ ደህንነቱ የተጠበቀ ወደሚባል ደረጃ ይቀንሳሉ።
- መጫወቻዎቹን በክሎሪን ማንጫ ፈሳሽ ውስጥ ይንከሩ፤ ትክክለኛውን መጠን ለማግኘት የ Department of Health (DOH፣ የጤና ጥበቃ መምሪያ) በማንጫ ኢንፌክሽን እና ቆሻሻ የማስወገድ መመሪያዎችን ይመልከቱ። የቤት ውስጥ የጎማ ጓንቶች በማጥለቅ ቆዳዎን ይጠብቁ።
- መጫወቻዎች ሙሉ በሙሉ እንዲደርቁ ይፍቀዱ (ለምሳሌ ሌሊቱን ሙሉ) ወይም መጫወቻዎችን በወረቀት ፎጣ ከመጥረግዎ በፊት የ 2 ደቂቃ የንክኪ ጊዜ ይፍቀዱ።
- ከማንጫው ፈሳሽ የሚወጣው ክሎሪን ከመጫወቻዎቹ ላይ ተንኖ ይሄዳል ስለዚህ ምንም የሚቀር ነገር አይኖርም እና ተጨማሪ እጥበት አያስፈልግም።

## መጫወቻዎችን በእቃ ማጠቢያ ማሽን ማጠብ

- እንደ እንጨት፣ ፕላስቲክ ወይም ብረት ያሉ አንዳንድ ጠንካራ መጫወቻዎች በእቃ ማጠቢያ ማሽን ውስጥ ሊታጠቡ ይችላሉ።  በመጫወቻዎች ላይ መመሪያዎችን ይመልከቱ።
- በአምራቹ የሚመከረውን ተገቢመጠን መጠን ያለው የእቃ ማጠቢያ ንፁህ ማድረጊያ ይጠቀሙ።
- መጫወቻዎችን ሙሉ በሙሉ በማጠብና በማድረቅ ዑደት ውስጥ ያስገቡ።
- መጫወቻዎችን በቆሸሹ ሳህኖች፣ ዕቃዎች፣ ወዘተ አይጠቡ።

## መጫወቻዎችን በማጠቢያ ማሽን ማጠብ

- ከጨርቅ የተሠሩ ብዙ ለስላሳ መጫወቻዎች ለምሳሌ የጨርቅ እንስሳት፣ የጭፈራና የማስመሰያ ልብሶች በማጠቢያ ማሽን መታጠብ ይችላሉ። በመጫወቻዎች ላይ መመሪያዎችን ይመልከቱ።
- ትኩስ ውኃና ንፁህ ማድረጊያ ይጠቀሙ።
- መጫወቻዎችን በተቻለበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ በሙቅ ማድረቂያ ያድርቁ።

ማሳሰቢያ:- የክሎሪን ማንጫን ከሌሎች ማጽጃዎች ወይም ኬሚካሎች ጋር እንዳይቀላቅሉ። ክሎሪንን ከአሞኒያ ጋር መቀላቀል አደገኛ ጭስ ያስከትላል። ከየክሎሪን ማንጫን ከቀዝቃዛ ውሃ ጋር ብቻ ይቀላቅሉ